# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 119 ነሃሴ 20 ቀን 2002 ገጽ 1


**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**"የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!."**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ "እምቢ ለመብቴ!!!" ብቻ ነው**

## የወያኔው የ5 አመት የኢኮኖሚ ልማት ትራንፎርሜሽን እቅድ የህልም እንጀራ ነው ሲሉ ታዋቂ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች አጣጣሉት

በቅርብ ቀን ይፋ የሆነው የአምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ የአምስት ዓመታት የልማት ግብ ርቆ የተሰቀለ ዳቦ ወይንም የህልም እንጀራ ነው እየተባለ መተቸቱን የገለጸው የቪ ኦ ኤ ው አማርኛ ክፍል በአምስት አመቱ የልማት መርኃ ግብር ዙሪያ በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ መምህር የሆኑትን ዶ/ር ጌታቸው በጋሻውንና በአለም ባንክ ከ30 አመታት በላይ በከፍተኛ አማካሪነት የሰሩትና በኢትዮጵያ ድህነትን ለማጥፋት የሚቻልበትን መንገድ የሚያመላክት መጸሃፍ በቅርቡ ለንባብ ያበቁትን ዶ/ር አክሎግ ቢራራን አነጋግሯል።

ቀደም ብሎ አምባገነኑ መለስ «አስር ከመቶ እናድጋለን ስንል እንደ እብድ ታይተን ነበር እኛ ግን ከዚያም በላይ አሳክተናል ፤ ከዚህ በላይ ከሰራን ደግሞ የበለጠ ውጤታማ እንሆናለን፤ ልምዱና አቅሙ አለን » ማለቱን አስመልክቶ አስተያየታቸውን የተጠየቁት ኢኮኖሚስቶቹ በሰጡት መልስ የስካሁኑ የኢትዮጲያ የእድገት አሃዝ በርካቶችን እያወዛገበ ይገኛሉ ካሉ በኋላ የማንኛውም ሃገር በሰባትም ይባል በ11 ነጥብ እድገት አሳይቻለሁ ሲል ይህ አባባል ሁሌም ከህዝብ ኑሮ መሻሻል ጋር ሊታይ ይገባዋል ብለዋል። በመቀጠልም እድገት በጥቂት የኢኮኖሚ ዘርፎች ሊመዘገብ ይቺላል ነገር ግን የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መሰረት ምንድነው የሚለው ጥያቄ በጣም መሰረታዊና አንገብጋቢ የሆነ ጥያቄ ነው ካሉ በኋላ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ደግሞ በግብርና ላይ የተመሰረተ ነው፤ ስለግብርና ስናወራ ደግሞ ትንንሽ የሆኑ አምራቾችን ይመለከታል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ከቢፒአር. በኋላ የመንግስት ተቋማት አገልግሎቶች ብቃት እና ጥራት ቀንሷል ተባለ

የአዲስ አበባ ዘጋቢ ሰሞኑን በላከልን ዜና ወያኔ ሊቃወሙኝ ይችላሉ ብሎ የሚሰጋቸውን ሰዎች ከመንግሥት መሥሪያቤቶች ለመመንጠር የተጠቀመበት የቢፒአር ፖሊሲ ቀደም ሲል አገልግሎታቸው ደካማ የነበሩትን መንግሥታዊ ተቋማትን ይበልጥ እየገደለ መሆኑንን ለተቋሞቹ ቅርበት ያላቸው በርካታ ሰዎች ቅሬታ እያሰሙ መሆናቸው ታውቆአል።

የወያኔ የአገዛዝ ሥር ዓቱን በመላው አገሪቱ ለማስፈንና ጸረ አገሪ ዕቅዱን ለማስፈጸም በቂ የሥልጣን እድሜ ለማግኛ የተጠቀመበት ቢ.ፒ.አር. ወይም "ቢዝነስ ፕሮሰሲንግ ሪቪው"ስለአገራቸውና ህዝባቸው በሚጨነቁ ሌሎች አገራት ደካማ አሰራርን ለማስወገድን በምትኩ ምርታማና ቀልጣፋ የሆነ አሰራር በሥራ ላይ ለማዋል ረድቶአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የአዲስ አበባው ሸራተን ሆቴል በድህነት ኑሮ በአካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን ማፈናቀሉን ቀጠለ

ካፒታል የዜና ምንጭ ከአዲስ አበባ እንደዘገበው፤ ከዘረኛው የወያኔ ቁንጮ ባለስልጣናት ጋር ልዩ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ትስስር አለው የሚባለው የሸህ አላሙድን ንብረት የሆነው ሸራተን አዲስ በሆቴሉ አካባቢ ይኖሩ ከነበሩት ነዋሪዎች ጋር ለረዥም ጊዜ ሲካሰስበት የነበረውን 42 ሄክታር መሬት አሸንፎ የግንባታ ሥራውን እንደሚጀምር ታውቆአል። እንደ ካፒታል ዘገባ ከሆነ ስምምነቱ የተደረሰው ያካባቢው ነዋሪዎች ከፍላጎታቸው ውጭ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ወደተገነቡት ኮንዶሚኒየም ቤቶችና ወደተዘጋጁላቸው መሬቶች እንደሚሄዱ ቃል ከተገባላቸው በኋላ ነው። ያካባቢውን ነዋሪዎች ያናገረው ዘጋቢያችን እንደገለጸው ከዚህ ቀደም ሸራተን አዲስ በተገነባበት ወቅት የተፈናቀሉ የአካባቢው ነዋሪዎች በድህነት አቅማቸው የፈለጉትን ሊያገኙና ልጆቻቸውን ለማስተማር አቅማቸው ወደማይችልበት የሲኤምሲ አካባቢ በመስፈራቸው እስከአሁን ድረስ ከነሙሉ ቤተሰባቸው እየተሰቃዩ መሆናቸውን ለሚየስታውስ ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ምን ያህል ለድሃው ህብረተሰባችን ደንታ እንደሌለው ያሳያል ብለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

**ግዜ** ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ በስዊድን ያለውን የኢትዮጵያ ኤምባሲ መዝጋቱ ጸረ-ኢትዮጵያዊ አቋሙን የሚገልጽ ነው ተባለ

ዘረኛውና አምባገነናዊው መለስ ዜናዊ ረቡእ ነሐሴ 5 ቀን በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ፣ በስዊድን የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኤምባሲ እንደሚዘጋ መናገሩ ይታወሳል። ጉዳዩን በሚመለከት አርብ እለት ለዝግጅት ክፍላችን መልክት የላኩ የፖለቲካ ተንታኝ ይህ የመለስ ውሳኔ ጸረ-ኢትዮጵያ አቋሙን የሚያንጸባርቅ ነው ብለዋል።

መለስ ዜናዊ ኤምባሲውን ለመዝጋት የወሰነበትን ምክንያት ሲገልጽ በስዊድን እና በኢትዮጵያ መካከል የልማት ትብብር እና ኢትዮጵያን የሚጠቅም ንግድ እንደሌለ ተናግሯል። ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየታቸውን የላኩት የፖለቲካ ተንታኝ ስዊድን ከኢትዮጵያ ጋር ባላት ከመቶ አመት ያለፈ ግንኙነት ለአገራችን ከፍተኛ ውለታን መዋሏን አስታውሰው፤ መለስ በሁለቱ አገራት መካከል የልማት ትብብር የለም ማለቱን "ነጭ ውሸት" ብለውታል። አምባገነኑ እንደ ስዊድን ካለች የረዥም ዘመን ወዳጅ ጋር አገራችንን ለማቆራረጥ የወሰነው ውሳኔ የጸረ-ኢትዮጵያ አቋሙ መገለጫ ነው ብለዋል።

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ባለፈው ሳምንት በተለያዩ የኢትዮጵያውያን ድረ-ገፆች ላይ የወጡ ትንታኔዎች መለስ ዜናዊ ኤምባሲውን ለመዝጋት የተነሳሳበት እውነተኛው ምክንያት ስዊድን ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የፖለቲካ ሁኔታ፣ በተለይም የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን እስር በሚመለከት፣ በአገዛዙ ላይ ከፍተኛ ጫና ማድረግ በመቀጠሏ ነው የሚል አመለካከት አዝለዋል።

## ቢሳካለት ለአቅመ አዳም ከደረሰው ኢትዮጵያዊ ውስጥ ግማሽ የሚሆነው ስደትን እንደሚመርጥ ጥናቶች አረጋገጡ

ኢትዮጵያን ጨምሮ በአንድ መቶ አርባ ስምንት ሃገራት ላይ በተደረገ ጥናት አገርን ለቆ በስደት የመኖር እድሉን ቢያገኝ 46 በመቶ የሚሆነው ለአቅመ አዳም የደረሰ ኢትዮጵያዊ ሃገሩን እየጣለ ወደስደት ዓለም መግባትን እንደሚመርጥ በቅርብ ቀን የወጣ ጽሁፍ አረጋገጠ። ይህን ጥናት ያካሄደው የሰው ልጆችን ባህሪ በማጥናት የ75 ዓመታት ልምድ ያለው ጋሉፕ በመባል የሚታወቀው ድርጂት ነው።

ይህ ድርጂት ባወጣው ጽሁፍ እንደተገለጸውና በቅርብ ቀን የተካሄደውም ጥናት እንደሚያረጋግጠው በጥናቱ ከተካተቱት 148 ሃገራት ውስጥ ኢትዮጵያ በቀዳሚነት ከሚገኙት ጥቂት ሃገራት ውስጥ እንደምትካተት ገልጿል። ዜጎቻቸው ስደትን በመምረጣቸው ከኢትዮጵያ ተርታ ከተሰለፉት ሃገራት ውስጥ ሃይቲ፤ ዚምባብዌ፤ ናይጀሪያና መንግስት የለሿ ሶማሊያ ይገኙበታል.። ባንጻሩ ዜጎቻቸው ስደትን የማይፈልጉ ናቸው በመባል የቀዳሚነቱን ስፍራ ከያዙ ሃገራት ውስጥ ሲንጋፖር፤ ንውዚላንድ፤ ሳውዲ አረቢያ፤ ካናዳ፣ ስዊትዘርላንድና ኩየት እንደሚገኙበትም ታውቋል።ከዚሁ ጋር በማያያዝ የጥናት ጽሁፉ እንደገለጸው ለነኝህ ስደተኞች የማረፊያ ቦታነቱን ቅድሚያ የምትወስደው ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ መሆኗን ይኸው መግለጫ አክሎ አስታውቋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ ስርአት የለም ወደፊትም አይኖርም ሲል ተመጻደቀ

የቪኦኤ አዲስ አበባ ዘጋቢ ፒተር ሄንሌይን በኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ ሲስተም ስለመኖሩ ላቀረበለት ጥያቄ፤ ውሸት የማይሰለቸው ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ አይኔን ግምባር ያርገው በሚል የተለመደ ቅጥፈቱ "እንደጃፓንና ቦትስዋና አንድ ጠንካራ ፓርቲ እንጅ የአንድ ፓርቲ ስርአት የለም" በማለት ተመፃድቋል። በጃፓንም ሆነ ቦትስዋና ለረጂም ጊዜ ስልጣን ላይ የቆዩት ፓርቲዎች በሃገራቸው ውስጥ በሰፊው የህዝብ አመኔታን አግኝተው የህዝብ ድምጽ ማጭበርበር ሳያስፈልጋቸው ወይንም በህዝብ የተመረጡትን መግደል፤ ማሰርና ከሃገር ማሰደድ ሳያስፈልጋቸው ስልጣን ላይ የቆዩ ኡሁን እንጂ እንደ መለስ ዜናዊና ቢጤዎቹ ግለሰቦች ለአስርና ላሃያ ዓመታት በስልጣን ላይ የቆዩበት ወቅት አልተመዘገበም ።

ከዚህም ሌላ የመናገር የመሰብሰብ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን መገደብ ሳያስፈልጋቸው የሃሰት የልማት እድገት ቁጥር ሳይፈበርኩ በአለም ዘንድ ዝናን ያተረፈ መሰራታዊ የእድገት ለሃገራቸው ያስመዘገቡ መሆኑን መለስና ቢጤዎቹ ልብ ብለውት አያውቁም ተብሏል። መለስ ዜናዊ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኛ “ትራንስፎርሜሽን ፕላን” ኢትዮጵያን ከዘረኝነት ማጽዳት ነው!!!

አንድን ነገር ደጋግሞ እየሠራ የተለየ ውጤት የሚጠብቅ አዕምሮው በትክክል የማይሠራ ሰው ብቻ ነው ይባላል። ወያኔ አዕምሮዓቸው በትክክል መሥራት በማይችል ሰዎች የተሞላ ድርጅት መሆኑ ድርጊቱ ይመሰክራል። ባለፉት አምሳ ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ሲደረግ የቆየው በባዶ ቁጥሮች በተነፋ እቅድ የመኩራራትን “ስልት” ዛሬ እነ ግርማ ብሩ እንደ አዲስ ጥበብ ያስተዋውቁን ይዘዋል። የወያኔ የሰሞኑ ማደንቆሪያ “አዲሱ” የአምስት ዓመት እቅድ “ትራንስፎርሜሽን ፕላን” በመባል ፈረንጅና ስም እንዲኖረው ከመደረጉ በስተቀር በይዘትም ሆነ በቅርጽ ከድሮዎቹ የባሰ እንጂ የተሻለ ነገር የለበትም።

የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ እቅድ ታሪክ መለስ ብሎ ለተመለከተ በተመሳሳይነታቸው መገረሙ አይቀርም። ሁሉም ወረቀት ላይ የሚጮኹ ናቸው። ሁሉም የየጊዜው ባለሥልጣኖች ጉራቸውን ነዝተውባቸዋል። ይሁንም እንጂ አንዳቸውም እናሳካለን ያሉትን ግማሹን እንኳን ተግባራዊ አላደረጉም። በተለይም ባለፉት ሠላሳ አመታት እቅዶቹ ብቻ ሳይሆን አቃጆቹም አልተቀየሩም። ለምሳሌ ግርማ ብሩ፣ መኮንን ማንያዘዋል እና ሱፍያን አህመድ የደርግ ማዕከላዊ ፕላን ባለሥልጣናት በነበሩበት ጊዜ በአየር ላይ የተንሳፈፉ እቅዶችን እየነደፉ ስለፈጣን ልማት አይቀሬነት “በደርግኛ” ሲተነትኑ ነበር። ዛሬ ያው የሰለጠኑበትን የውሸት እቅድ “አጠናክረው” “በወያኔኛ” መተንተን ተያይዘውታል። እነዚሁ ሰዎች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ውስጥ ስለመሆኑ ቢያንስ በሶስት የተለያዩ ጊዜያት ተናግረዋል። የመጀመሪያው የደርግን የአስር ዓመት እቅድ ሲያስተዋውቁ የተናገሩት ሲሆን፤ በዘመነ ወያኔ ደግሞ ይኸ ሁለተኛ ጊዜዓቸው ነው። ዘወትር ተግባራዊነቱ የማይታይ “የመዋቅራዊ ለውጥ እቅድ” አጋፋሪዎች ሆነው መቅረታቸው ህሊናቸውን አይኮሰኩሰውም። “እናመጣለን ብላችሁት የነበረው እድገት የታል?” ብሎ የጠየቃቸው ስለሌለ ውሸትን ከመለማመድ አልፈው ከአጥንትና ሥጋቸው ጋር አዋህደውታል። ይብዛም ይነስ ያላቸውን የአካዳሚና የአስተዳደር እውቀት እየቀለበ ለሚጋልባቸው አምባገነን ሁሉ መጠቀሚያ አድርገውታል። እናም አሁን ለበለጠ ውሸት ተበረታተው ቀርበዋል። ከእነዚህ ሰዎች የተሻለ የአድርባይነት ህያው ተምሳሌት ከየት ይገኛል?

አሁን የታወጀው “የትራንስፎርሜሽን እቅድ” በዘፈቀደ ከተሞሉ ቁጥሮች በስተቀር መሬት ባለ ሃቅ ላይ ላለመመሥረቱ በርካታ ጥያቄዎችን በማንሳት ማረጋገጥ ይቻላል። “ምን ተደርጎ ነው ኢኮኖሚው በአንድ ጊዜ እንዲህ የሚመነደገው?” የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ነው። ማንም እንደሚረዳው የአገር ኢኮኖሚ በአንድ ምሽት በቅሎ የሚያድር እንጉዳይ አይደለም። ለእንጉዳይም ቢሆን ደመናና ካፊያ ያስፈልገዋል። አሁን እየተነገረን ያለው እድገት ምንጩ እምን ላይ ነው? ይህ ጥያቄ በተደጋጋሚ ተነስቶ መልስ ባለማግኘቱ ወደ ሌሎች ጥያቄዎች እናልፋለን። ወያኔዎች እንዲህ በቀላሉ መመንደግ እንደሚቻል እያወቁ ምነው እስከዛሬ ተንቀረፈፉ? ለምንድነው ባለፈው አምስት ዓመት የታቀደውን ግማሽ ያህል እንኳን ሰብል ያልተሰበሰበው? ከ16. 7 ሚሊዮን ቶን ወደ 38.21 ሚሊዮን ቶን እናሳድጋለን ተብሎ ታቅዶ 18.08 ሚሊዮን ቶን ላይ ሲቆም ማን ተጠየቀ? ለምንድነው የኢንዱስትሪው ድርሻ 16.5 ከመቶ ይሆናል ተብሎ ታቅዶ ድሮ ከነበረበት 13.6 ከመቶ ወደ 13 ከመቶ ያሽቆለቆለው? ባለፉት አምስት ዓመታት ያልሰራው እቅድ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት እንደሚሠራ በምን ተገመተ? ጥያቄዎቻችን ብዙ ናቸው። የአፋር ክልል አምስት ሚሊዮን ተማሪዎችን አስመዘገበ እያለ ከሚቀደድ የዋሾዎች ቡድን እርባና ያለው ምላሽ ይገኛል ተብሎ ስለማይጠበቅ ጥያቄዎቻችንን እዚሁ ላይ ማብቃቱን መርጠናል።

አንድ ሃቅ ግን አጽንዖት ሊሰጠው ይገባል። ይህም “የአምስት ዓመቱ የትራንስፎርሜሽን ፕላን” የውሸት ክምር መሆኑ ነው። ከውሸትነቱ በተጨማሪ ግን ይህ እቅድ ከዚህ በፊት ከነበሩት ሁሉ የበለጠ ለኢትዮጵያ አደገኛ ነው። ይህንን በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርጎ ማየት ይበጃል።

ወያኔ በዘር የተከፈለች ሁለት ኢትዮጵያዎችን ፈጥሯል። አንደኛዋ ኢትዮጵያ የወያኔዎችና የምስለኔዎቻቸው ነች። ይህች አገር ሃብታምና በከፍተኛ ፍጥነት እያደገች ያለች ናት። የዚች አገር ዜጎች ቁጥር ከጥቂት መቶ ሺዎች አይበልጥም። ሌላኛዋ ኢትዮጵያ 80 ሚሊዮን ያህል እንሆናለን ተብሎ የምንገመተውን የያዘችው ምስኪኗ እማማ ኢትዮጵያ ናት።

ሃብታሟ ኢትዮጵያ በዓመት 3.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እርዳታ ስለምታገኝ በዓመት 15 በመቶ ማደግ ያንሳታል። እርግጥ ነው እርዳታ የሚመጣው በድሃዋ ኢትዮጵያ ስም ነው። ይሁን እንጂ የሃብታሟ ኢትዮጵያ “ምርጥ” ዜጎች አንዱ በተቋራጭነት፣ ሌላው በእቃ አቅራቢነት፤ አንዱ በደላላነት፣ ሌላው በአስፈፃሚነት ቢሊዮኖቹን ዶላሮች ይከፋፈሉታል። የውጭ እርዳታ እና “በምርጥ ዜጎች” መካከል ያለው የሃብት ክፍፍል እንዲቀጥል መንገዶች መሠራት፤ ግድቦች መገንባት አለባቸው - አለበለዚያማ ምን በምን ሰበብ ሊወሰድ ኖሯል?

በከተሞች አዳዲስ ፎቆችና ቪላዎች መገንባታቸውም እሙን ነው። ሆኖም አሁንም እነዚህ ፎቆችና ቪላዎች የእነማን ናቸው ብሎ መጠየቅ ያሻል። መልሱም ቀላል ነው - ንብረትነታቸው የሃብታሟ ኢትዮጵያ ዜጎች ነው። በድሆች መንደር ውስጥ የዱባይ ህንፃ መንትያዎች ቢገነቡ የመበላለጣችን እንጂ የመልማታችንን መጠን አያመለክቱም።

የሃብታሟ ኢትዮጵያ ዜጎች ሃብት በአገር ውስጥ ብቻ አይደለም ያለው። እነዚሁ ሰዎች በአውሮፓ፣ በአሜሪካ እና በአረብ አገሮች የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን እያከማቹ ነው። አዜብ መስፍን፣ ስብሃት ነጋ፣ ሳሞራ የኑስ፣ ገዛኢ አበራ፣ አርከበ እቁባይ፣ አባይ ፀሃዬ፣ አባዱላ ገመዳ፣ ኩማ ደመቅሳ እና መሰሎች በውጭ አገራት ያከማቹት ሃብት በመቶ ሚሊዮኖች የአሜሪካ ዶላሮች የሚገመት ነው።

የአብዛኞቻችን ኢትዮጵያ ግን እያደር እየከሳችና እየገረጣች ነው። የአብዛኞቻችን ኢትዮጵያ በድህነት፣ በበሽታ፣ በማይምነት፣ በፍትህ እጦት ዓለምን ትመራለች። ዜጎቿ አገር ለቀው እንዳይወጡ በር ተዘግቶባቸው የሚገኙ እስረኞችና ግዞተኞች ናቸው። ይህች ኢትዮጵያ በቅራኔዎች ተወጥራ ልትፈነዳ ደርሳለች። የሁለተኛዋ ኢትዮጵያ ዜጎች መሬት በአንደኛ ኢትዮጵያ ዜጎች እየተነጠቁ ገበሬዎች ለቀን ሠራተኝነት እንኳን የወያኔ አባልነት ፎርም በመሙላት ተገዢነታቸውን እንዲያረጋግጡ የሚገደዱባት አገር ናት።

ታድያ የሶፍያን አህመድና ግርማ ብሩ “የትራንስፎርሜሽን ፕላን” የየትኛዋ ኢትዮጵያ እቅድ ነው? ሃብታሟ ኢትዮጵያ “ትራንስፎርም” ከሆነች ቆይቷል፤ ደግሞ 15 ከመቶ ያንሳታል። የኛዋ ኢትዮጵያ ግን ስለምን እየተነገረ እንደሆነም አይገባትም። እሷ በሰቆቃ፣ በእልህና በቁጭት ተሞልታ ለውጥን በማማጥ ላይ ያለች ናት። ስለ “ኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን” ለመቀለድ ጊዜም ፍላጎትም አቅምም የላትም።

“የአምስት ዓመት የትራንስፎርሜሽን ፕላን” ነፋስ ላይ የቆመ በመሆኑ ከግርግር በስተቀር መሬት ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም። ሆኖም ከሌሎች ተመሳሳይ እቅዶች ይኸኛው የከፋ የሚያደርገው በሌሎች አገሮች እርዳታ በትንሹ እንኳን ቢሳካ ጥቂት ዘረኞችን ጠቅሞ አብዛኛዎቻችንን የሚጎዳ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ለማናችንም አይበጅም።

ኢትዮጵያ በሁለት ተከፍላ መቆየት አትችልም። “ትራንስፎርም” መደረግ ያለበት እውነታ ይህ ነው:: የኛ ትራንስፎርሜሽን ፕላን ዘረኝነትን በማጥፋት ኢትዮጵያን የሁሉም ዜጎቿ የእኩል አገር ማድረግ ነው። ይህ ደግሞ ይቻላል፤ እናደርገዋለንምም!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### የአዲስ አበባው ሸራተን ሆቴል በድህነት ኑሮ . . . (ከገጽ 1 የዞረል)

የሚፈናቀሉት ያካባቢው ነዋሪዎች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተገባላቸው ማካካሻ በቂ አይደለም በማለት እሮሮ ሲያሰሙ የቆዩ ሲሆን የሚመለከታቸው የአራዳ እና የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ሃላፊዎች በየቀበሌው ጊዜያዊ መኖሪያ እናዘጋጃለን፣ ኮንዶሚኒየም ቤቶችን እንድታገኙም ቅድሚያ እድል እንሰጣለን ካሉ በኋላ ጊዜያዊ ስምምነት ተደርሶ ነበር.፡ ይሁን እንጂ ኮንዶሚኒየም ቤቶችን ለመግዛት የቤቶቹን 20 በመቶ ዋጋ ቅድሚያ መክፈል እንዳለባቸው ሲታሰብ ከአብዛኛዎቹ ነዋሪዎች የገቢ ምንጭ አንፃር የማይታሰብ ከመሆኑም በላይ ባለፉት ሃያ አመታት ተመሳሳይ ቃል ተገብቶላቸው የተፈናቀሉ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ የከተማይቱ ነዋሪዎች እስከዛሬም ድረስ ከዝናብም ሆነ ከብርድ ሊያስጥሉ በማይችሉ ጊዜያዊ መጠለያዎች ውስጥ እስከነ ህጻን ልጆቻቸውና ጧሪ የሌላቸው አዛውንት ቤተሰቦቻቸው ጋር ተጥለው የቁም ስቃይ ህይወት እየገፉ እንደሚገኙ ለማረጋገጥ ተችሎአል።

ከተፈናቃዮቹ አብዛኞቹ አሁን ለመልቀቅ በተገደዱበት መኖሪያ ቤት ውስጥ ተወልደው ያደጉ እና የኑሮ መሠረታቸውንም እዚያው ያደረጉ እንደሚገኙ ሲታወቅ ለንብረታቸው ዋጋ በአሁኑ ሰአት ባለው የገበያ ሂሳብ እንዲገመትላቸው ቢጠይቁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግን ከዋጋ በታች እጅግ ያነሰ ካሳ እንዲቀበሉ ስለፈረደባቸው በምትኩ በተሰጣቸው ሌላ መሬት ላይ አዲስ ቤት ለመገንባት የማያስችላቸው መሆኑ ታውቋል። ከቦታው ከህሊና ግምት የበዛ ትርፍ ለማትረፍ ድሆችን እያባረረ ያለውና በአፍቃሪ ወያኔነቱ ያለውና በአፍቃሪ ወያኔነቱ አንቱታን ያተረፈው የሸራተን አዲስ ሆቴል ባለቤት ሙሃመድ አላሙዲ ለቦታው ተገቢ የሆነውን ማካካሻ መክፈል እንዳለበት ህሊናው ያስገድደዋል ተብሎ የሚገመት ባይሆንም ለድሃው ቆሜያለሁ እያለ በቁጥጥሩ ስር ባሉት ሚዲያዎች ሌት ከቀን እየወተወተ ያለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ተባባሪ በመሆን ካቅም በታች እንዲገመትና እንዳይሆን ማድረጉ የሚያሳየው ሁለቱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፆች መሆናቸውን ነው ሲሉ ዘጋቢያችን አስተያየት የጠየቃቸው ነዋሪ ገልጸዋል።

### ከቢ.ፒ.አር. በኋላ የመንግስት ተቋማት . . . (ከገጽ 1 የዞረል)

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ግን በሰራተኞች ብቃት እና ትምህርት ፈንታ የፖለቲካ አመለካከቶቻቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት አይደግፉኝም ብሎ የገመታቸውን በማባረር ተቋማቱን በካድሬዎቹ እና በግዳጅ የፓርቲ አባላት ማስወረሩ ይታወቃል።

ዘጋቢያችንን ተዘዋውሮ ያናገራቸው አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፥ በተለይም ወደ መንግስት ሆስፒታሎች መሄድ በሽታ የሚጨምር ሆኗል ብለዋል። እርጉዝ ሴቶችን ጨምሮ በርካታ የመንግስት ሆስፒታሎች እና ጤና ጥበቃ ተጠቃሚዎች ስላሽቆለቆለው የአገልግሎት ደረጃ አማረው፤ ይህም ልምድ ያላቸው የቀድሞ ሰራተኞች መባረራቸውን ተከትሎ ከተከሰተ መመሰቃቀል ጋር የተያያዘ ነው ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ከአንድ ዘር የተውጣጣ የገዢ መደብ ለመፍጠር ሌት ከቀን የሚሰራው የወያኔ ቡድን ለኢትዮጵያችን መልካምን ለማድረግ አይቻለውም! *(ከዝግጂት ክፍላችን)*

በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር የምትገኘው አገራችን ኢትዮጵያ ከሰሞኑ ብዙ የድህነት ሽልማቶችን ተቀብላለች።

ዴሞክራሲ እና እኩልነትን የማስፈን ጭንብሎቹ የወደቁበት ዘረኛ አገዛዝ ህልውናውን ለማስጠበቅ ሲል "ልማት ልማት" የሚለውን ዘፈን መዝፈን እና ማስዘፈን ከጀመረ እንደሰነባበተ እናውቃለን። በተለይም የምርጫ 97 ሽንፈቱን ተከትሎ ክፉኛ የታመመው አገዛዝ አገሪቱ የሌላትን እና በየመንግስት ባንኩ ጥረው ግረው ያገኙትን ገንዘብ ካስቀመጡ ኢትዮጵያውያን የበዘበዘውን ገንዘብ በንግድ ድርጂት ስም ላስመዘገባቸው የራሱ ድርጂቶች በማበደር አዲስ አበባን ህንፃ በህንፃ ካደረገ በኋላ፤ እነዚህ ሰው ሰራሽ የድንጋይ ክምሮች የአንድን አገር እድገት ለብቻቸው የሚገልጹ ይመስል፤ እንደ ልማት ማስረጃ አድርጎ ሲያስነግርላቸው እንደቆየ እናውቃለን።

ዘረኛው አገዛዝ ፈርዶበት ግን የሰለጡኑ አይኖች ሞልተው ኖሯል፤ ከህንፃዎቹ በስተጀርባ እየሄዱ የሚፈትሹ እየተበራከቱ መጡ። ወያኔ የእድገት ወሬውን የሚያቆመው ከተቀቀሉ ቁጥሮች በተሰራ መሰረት ላይ መሆኑም ተጋለጠ። ይሁን እንጂ "የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ" እንዲሉ...እርቃኑን በመውጣቱ መግቢያ ጉድጓድ ያጣው አገዛዝ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት የልማት ከበሮውን ማስደለቁን ቀጥሎበታል።

ከኢትዮጵያ ህዝብ በተዘረፈ ገንዘብ ከርሳቸውን እየሞሉ በአለማችን አራት ማእዘናት ተሰራጭተው ያሉ የወያኔ ጭፍሮችም ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል በሚል እምነት "እድገት እድገት እድገት" እያሉ ይዘምራሉ። የወያኔ የእድገት ወሬ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዘንድ እንደ ቀልድ የሚታይ ጉዳይ ነው። ከጥቂት አመታት በፊት በግ እያረደ የሚፈስከው ቤተሰብ ሁለት ኪሎ ስጋ መግዛት ተስኖት እራሱን ሲያገኝ፤ ሽሮም ብትሆን በየቀኑ በልቶ ማደርን የለመደው ደግሞ ምግብ በፈረቃ መብላት እንደጀመረ እያወቀው "ልማት" የሚሉት ነገር ተቃራኒ ትርጉም ከሌለው በስተቀር ስላቅ እንደሆነ ደህና አድርጎ ያውቀዋል።

ከደጋፊዎቹ እና አድርባዮች በስተቀር የወያኔን የልማት መዝሙር ተቀባብለው ሲዘምሩ የከረሙት ጥቂት የዋሆች እና አይናቸውን ጨፍነው ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ አገዛዙን ለመደገፍ የሚፈልጉ አንዳንድ አገራት እና አለማቀፍ ተቋማት ናቸው። አሁን አሁን ግን አለማቀፉ ማህበረሰብ አይኑን እንደጨፈነ መቀጠል ወደማይችልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ነው። የወያኔን የተቀቀሉ ቁጥሮች እያጋለጡ ያሉ አንዳንድ ምእራባውያን ተመራማሪዎች ብቅ ብቅ እያሉ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ በዚሁ የሚቆም አይሆንም። የዘረኛው አገዛዝ ዴሞክራሲያዊነት ሃሰት መሆኑ ተጋልጦ አብዛኛው አለማቀፍ የመረጃ አውታር እንዳውገዘው ሁሉ የኢኮኖሚ ውሸቱም ሙሉ በሙሉ እርቃኑን የሚወጣበት ቀን እየተቃረበ ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር በአለማችን ላይ እጅግ ደሃ ከሚባሉት አገራት ውስጥ አንዷ እንደሆነች በቅርብ ጊዜ ካሳዩት ሪፖርቶች ውስጥ አንዱ እንግሊዝ አገር በሚገኘው ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ እና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትብብር ተዘጋጅቶ ይፋ የተደረገው ነው።

"መልቲ ዳይሜንሺናል ፖቨርቲ ኢንዴክስ" ወይም ዘርፈ ብዙ የድህነት መመዘኛ የሚባለውን አዲስ ዘዴ በመጠቀም በተደረገው በዚህ ጥናት፣ 90 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ደሆች እንደሆኑና ይህም በከፋቱ ከአለም ሁለተኛ ደረጃ መያዙን አስታውቋል። አንደኛውን ደረጃ የያዘችው ምእራብ አፍሪካዊቷ አገር ኒጀር ስትሆን መንግስት አልባዋ ሶማሊያ እንኳን በየአመቱ አስር በመቶ እድገት ተመዝግቦባታል ተብሎ መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ ከሚነግሩን ኢትዮጵያችን ተሽላ ተገኝታለች።

ከዚህ ቀደም በስራ ላይ ይውሉ የነበሩ የድህነት መመዘኛዎች፣ የግለሰቦችን የቀን ገቢ ብቻ ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ሲሆኑ፤ አዲሱ መመዘኛ በሰው ልጅ ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ዘርፈ ብዙ ጉድለቶችን ከግምት የሚያስገባ ነው። ከነዚህም ውስጥ የትምህርትና የጤና ጥበቃ ሁኔታ፤ እንዲሁም የአጠቃላይ ኑሮ ደረጃን ይለካል። በዚህ መሰረትም፥ ከአስር ኢትዮጵያውያን ዘጠኙ ድሆች ናቸው ሲል ሪፖርቱ ደምድሟል።

ጥናቱን ያካሄደው ተቋም ለምርምሩ የተጠቀመው ዳታ ወይም መረጃ የዛሬ አምስት አመት የተሰበሰበ መሆኑንም ገልጿል። ባለፉት አምስት አመታት፣ በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ የወያኔ አገዛዝ ስራ ላይ ያዋለውን ሃላፊነት የጎደለው የገንዘብ ፖሊሲ ተከትሎ፣ ቁጥራቸው የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን ቀድሞ ከነበረው ወደ ባሰ ድህነት መሸጋገራቸውን ከግምት ውስጥ ስናስገባ፣ ይህ ድህነት በምን ያህል እጅ እና በምን ያህል ጥልቀት ጨምሮ ይሆን ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

ኒውስዊክ የተባለው ታዋቂ የአሜሪካ መጽሔት ባለፈው ሳምንት ባወጣው ሪፖርት ደግሞ ለነዋሪዎቻቸው በሚሰጡት ምቾት እና እድል ላይ አንድ መቶ የአለም አገራት አወዳድሮ ኢትዮጵያን 94ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል።

መጽሔቱ፥ "ዛሬ ብትወለድ፥ የትኛው አገር በጤና፣ በደህንነት፣ በብልጽግና፣ እና በእድገት የተሞላ ኑሮ እንዲኖርህ ከፍተኛውን እድል ይሰጥሃል?" የሚለውን ጥያቄ ይዞ በመነሳት ንጽጽሩን እንዳካሄደ ገልጿል። ትምህርትን፣ ጤናን፣ የኑሮ ጥራት ደረጃን፣ የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነትን፣ እና የፖለቲካ ሁኔታን እንደማነፃጸሪያ ነጥቦች ተጠቅሟል። ለምሳሌ የኑሮ ጥራት ደረጃን ለመመዘን ከተጠቀመባቸው ቁልፎች ውስጥ አንዱ "በቀን ከሁለት ዶላር በታች" የሚያገኙ ዜጎች ቁጥር ሲሆን፤ 77.57% የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ከዚህ እንደሚመደቡ አስረድቷል። ይህ ሪፖርት አገራቱን ለማነፃጸር የተጠቀመው መረጃ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር 2008 እና 2009ን የሚሸፍን እንደሆነም ታውቋል።

በዚህ ሪፖርት መሰረት የምግብ ዋስትና እጥረት የከፋ ደረጃ ላይ ካለባቸው አስር የአለም አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ነች።

ይህንን ያለው ብሪታንያ በሚገኝ እና ሜፕልክሮፍት በተባለ ድርጅት፣ ከተባበሩት መንግስታት የአለም የምግብ ፕሮግራም ጋር በመተባበር፣ የሚዘጋጀው አመታዊ የምግብ ዋስትና አደጋ መለኪያ ሪፖርት ነው። ሪፖርቱ ወደ ድምዳሜ ለመድረስ አስራ ሁለት መመዘኛዎችን የሚጠቀም ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ የእህል ምርት፣ የነፍስ ወከፍ ገቢ፣ የግብርና እና የማከፋፈያ መሰረተ ልማት አውታሮች ጥራት፣ ግጭቶች፣ እንዲሁም የመንግስት ብቃት የሚሉት ይገኙበታል። በዚህም አኳኋን በአለም ላይ አደገኛ የምግብ ዋስትና እጥረት ካለባቸው አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያን ስድስተኛ ደረጃ ላይ አኑሯታል።

ይህ ሪፖርት የተሰራው ወያኔ የሚያወጣቸውን የእህል ምርት ቁጥሮች ተጠቅሞ ይሁን አይሁን ግልጽ አይደለም። ተጠቅሞ ከሆነ አደጋው የከፋ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ምእራባውያን ተመራማሪዎች ጥያቄዎች እያነሱ ያሉበት ዋና ጉዳይ ወያኔ በግብርናው ዘርፍ አለ የሚለው እድገት እና የሚሰጠው ቁጥር ነው።

በሌላም በኩል ጋላፕ የተባለ የጥናት ተቋም ባሰባሰበው መረጃ መሰረት እድሉ ቢቀርብላቸው 46 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ጥለው እንደሚሄዱ ገልጿል። አንዳንዶች ይሄ ከእውነተኛው ቁጥር እጅግ ያነሰ ነው ይላሉ።

የአንድን አገር ውስጣዊ ሁኔታ ከሚገልጹ ነገሮች ውስጥ አንዱ ሰዎች ወደ ውስጥና ውጪ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች አገር ጥለው የሚሰደዱ ከሆነ፣ በዛ አገር ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዳሉ ጠቋሚ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የፖለቲካ አፈና እና ድህነት የተነሳ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን በየአመቱ ቀዬያቸውን እየጣሉ እንደሚሰደዱ ይታወቃል። የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽን በሰኔ ወር ባወጣው ሪፖርት፥ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ2009 ብቻ 42500 ኢትዮጵያውያን በተለያዩ አገራት የፖለቲካ ጥገኝነት እንደጠየቁ መግለጹ ይታወሳል። ይህ ቁጥር እንግዲህ የፖለቲካ ጥገኝነት የጠየቁትን ብቻ የሚያካትት ነው። ስራ ፍለጋ ወደተለያዩ አገራት ህጋዊ እና ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ የሚሰደዱትን አያካትትም።

ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በአገራቸው ይመሩት የነበረው ኑሮ ምን ያህል እንዳንገሸገሻቸው የሚታወቀው ደግሞ ሌላ አገር ለመድረስ ሲሉ ሊያልፉበት የሚፈቅዱት መከራ ነው። የተሻለ ኑሮን ተስፋ እስካዘለ ድረስ ምንም አይነት መከራ ይሻላል ብለው የወሰኑ ይመስላሉ። ኑሮ በኢትዮጵያ ተስፋና ደህንነት የለውምና፤ ወደ ጣሊያን ለመሻገር በእግር ሲኳተን አሸዋ ውስጥ ሰጥሞ መቅረት ይሻላል።

በየቀኑ ዜና ለሚከታተል ሰው፥ በሆነ አገር ስለሚንከራተቱ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች የሚከተለውን መስማት የተለመደ ነው።

***"በየእለቱ ሊባል በሚቻል ሁኔታ የዜና ድረ-ገፆች ሲከፈቱ የሚታዩት ርእሶች፥ "ወደ የመን ሊያቋርጡ ሲሞክሩ የነበሩን ኢትዮጵያውያን ተሸክማ የነበረች ጀልባ ሰጠመች፤ የግብጽ ፖሊስ ወደ እስራኤል ለማቋረጥ ሲሞክር የነበረን ኢትዮጵያዊ ተኩሶ ገደለ፤ ከሁለት ሺህ የሚበልጡ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በታንዛኒያ እስር ላይ ይገኛሉ፤ ኢትዮጵያውያን ኢራቅ ውስጥ ስራ ይፈልጋሉ፤ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በደቡብ አፍሪካ ተደበደቡ፤ ኢትዮጵያዊት ሰራተኛ በአንድ የመካከለኛ ምስራቅ አገር ተገደለች፤ የመን 150 ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ወደ አገራቸው መመለሷን እና የኬንያ ፖሊስ በአንድ ቤት ውስጥ ታጭቀው የነበሩ 90 ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ማሰሩን ገለጸ የሚሉ እና የመሳሰሉት ናቸው።***

የወያኔ ባለስልጣናት እና ደጋፊዎች አገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ አስተያየቶች ሲሰጡ፥ "ሆዳቸውን በፈረንጅ ምግብ መሙላት አምሯቸው ነው" ይላሉ። "እድገት አምጥተናል፣ ሚሊዮኔር ገበሬዎች አፍርተናል" የሚሉን ሰዎች ዞር ብለው በቂ ምግብ አገር ቤት እንደሌለ በማመን እራሳቸውን የሚያጋልጡበት ምክንያት ግልጽ ባይሆንም፤ ምግብ ፍለጋ የትም መሄድ ግን ሃጢያት አይደለም።

ምግብ ከሶስቱ የሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ነው። የሰው ልጅ እነዚህን ፍላጎቶቹን ለማሟላት ነፍሱን እና ክብሩን እስካልሸጠ እና ሌሎችን እስካልጎዳ ድረስ ምግብ ፍለጋ መሰደድ ወንጀልም ሃጢያትም አይደለም። የሚያሳፍረው ግን ዜጎች ምግብ ፍለጋ ጥለዋት ይሚሄዱትን አገር ሃብትና ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው እየቦጠቦጡ ስደትን ማባባሱ ነው።

ዋናው ጥያቄ መሆን ያለበት ኢትዮጵያ ውስጥ ለምን በቂ ምግብ የለም የሚለው ነው? ኢትዮጵያ ውስጥ በቂ ትምህርት ለምን የለም? በቂ ስራስ ለምን የለም? በቂ እድልስ ለምን የለም? ፖለቲካዊ መብትስ ለምን አይከበርም?

እነዚህን ጥያቄዎች ለአገራችን የሚወግን እና ከህዝብ የፈለቀ፤ በህዝብ ለህዝብ የተሰራ ስርአት እስኪኖረን ድረስ መልስ አናገኝላቸውም ብቻ ሳይሆን መጠየቅም አንችልም። ሲጀመር ሊዘርፍ፣ ሊያስር፣ ሊገድል እና ሊያጠፋ ከመጣ ዘረኛ አገዛዝ ተጠያቂነትንም ሆነ ማንኛውንም አዎንታዊ ነገር መጠበቅ የዋህነት ነው። በወያኔ አገዛዝ ስር ልማት አለ የሚለው የአገዛዙ ወሬ ሃሰት መሆኑን ለማሳየት ብለን እንጂ ይህን ሁሉ የዘረዘርነው፤ ከዚህ አገዛዝ መልካምን ነገር እንጠብቃለን ለማለት አይደለም። ለዚህም ነው መከራችንና ስቃያችን እንዲያበቃ በተባበረ ክንድ ለዚህ ሰቆቃ የሚዳርጉንን ዘረኞች በትግላችን ማስወገድ ቅድሚያ ሊሰተው የሚገባ ነው የምንለው።

ጅቦች የበጎች እረኞች እንዲሆኑ ተፈጥሯቸው እንደማይፈቅድላቸው ሁሉ፤ ከአንድ ዘር የተውጣጣ የገዢ መደብ ለመፍጠር በርትተው የሚሰሩት የወያኔ መሪዎችም ለኢትዮጵያችን መልካምን ለማድረግ አይቻላቸውም!

## በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር የሚገኙ የህዝብ መገናኛ ብዙሃን የሚፈበርኩት ውሸት 'ከአሳፋሪነት ደረጃ እያለፈ ነው' ተባለ

በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር የሚገኙ መገናኛ ብዙሃን የሚፈበርኩት ውሸት ከአሳፋሪነት እያለፈ ነው ሲሉ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን አወገዙ።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ድረ-ገጽ በአፋር ክልል በመጪው አመት ትምህርት ቤት የሚገቡ ህፃናትን አስመልክቶ ያወጣው ዜና አነጋጋሪ ሆኖ ቆይቷል። ድረ-ገጹ በመጪው አመት በአፋር ክልል ከአምስት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ህፃናት ትምህርት ቤት እንደሚገቡ እና ይህም በክልሉ ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሽፋን ወደ ሃምሳ በመቶ ከፍ እንደሚያደርገው ዘግቧል።

በራሱ በአገዛዙ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ ማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ባወጣው ቁጥር መሰረት የአፋር ክልል አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አንድ ሺህ ዘጠና ሁለት ነው። በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ዘገባ መሰረት ግን በክልሉ ውስጥ ያሉት ህፃናት ቁጥር ብቻ ከሶስት እጥፍ በላይ የአጠቃላይ የህዝብ ቁጥሩን ይበልጣል።

በተጨማሪም፥ እንደ ዜና አውታር ተብዬው ዘገባ፥ በመጪው አመት ትምህርት ቤት ሊገቡ የተዘጋጁት አምስት ሚሊዮን ህፃናት የክልሉን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን ከፍ የሚያደርጉት ከ46 በመቶ ወደ 50 በመቶ፤ በአራት በመቶ ብቻ ነው። ይህ ማለት በአፋር ክልል ለትምህርት እድሜ የደረሱ ህፃናት ቁጥር 125 ሚሊዮን ነው ማለት ነው። ያ ደግሞ አሁን ካለው የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር እራሱ በአስርተ ሚሊዮን ይበልጣል።

ጉዳዩን በሚመለከት ለዝግጅት ክፍላችን ጥቆማን የላኩ ግለሰብ፥ በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኙ መገናኛ ብዙሃን ጉዳይ ከአሳፋሪነት አልፎ አስቂኝ ሆኗል ብለዋል። ሌላ አስተያየት ሰጪ ደግሞ ከዚህ ቀደም የአንድ ክልል ቢሮ ሃላፊ በክልሉ ክትባት ወስደዋል የተባሉ ህፃናት ቁጥር ከክልሉ ህዝብ ቁጥር የበለጠ እንደሆነ የሚያሳይ ሪፖርት ቀርቦለት እንደፈረመው መስማታቸውን ጠቅሰዋል።

ይህ የሃሰት ዘገባ ኢትዮጵያን ሪቪው በተባለ ድረ-ገጽ ላይ ከተጋለጠ የተወሰኑ ሰዓታት በኋላ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ምንም ማስተካከያ ሳያውጅ እና ይቅርታ ሳይጠይቅ ዘገባውን ከድረ-ገጹ እንዳስወገደ ለማወቅ ችለናል።

## ኢትዮጵያ በአለም ላይ የምግብ ዋስትና እጥረት ካለባቸው አስር ዋና አገሮች ውስጥ አንዷ ነች ተባለ

የምግብ ዋስትና እጥረት የከፋ ደረጃ ላይ ካለባቸው አስር የአለም አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ነች መባሉን አዣንስ ፍራንስ ፕሬሽ የተባለው የዜና አውታር ዘግቧል።

የዜና አውታሩ እንደ ምንጭ የጠቀሰው ብሪታንያ በሚገኝ እና ሜፕልክሮፍት በተባለ ድርጅት፣ ከተባበሩት መንግስታት የአለም የምግብ ፕሮግራም ጋር በመተባበር፣ የሚዘጋጀውን አመታዊ የምግብ ዋስትና አደጋ መለኪያ ሪፖርት ነው። ሪፖርቱ ወደ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት አስራ ሁለት መመዘኛዎችን እንደሚጠቀም የታወቀ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ የእህል ምርት፣ የነፍስ ወከፍ ገቢ፣ የግብርና እና የማከፋፈያ መሰረተ ልማት አውታሮች ጥራት፣ ግጭቶች፣ እንዲሁም የመንግስት ብቃት የሚሉት ይገኙበታል። በዚህም አኳኋን በአለም ላይ አደገኛ የምግብ ዋስትና እጥረት ካለባቸው አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያን ስድስተኛ ደረጃ ላይ አኑሯታል።

በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር የምትገኘው ኢትዮጵያ በየአመቱ በሚወጡ የተለያዩ የድህነት እና የኑሮ ደረጃ መመዘኛዎች ላይ አሉታዊ ውጤቶች የምታስመዘግብ የአለም ጭራ መሆኗ ይታወቃል። የወያኔ አገዛዝ እድገትን እያስመዘገበ እንዳለ ሁልጊዜ ቢደሰኩርም በአገሪቱ ውስጥ ያለው እውነታ ግን ከዛ የራቀ እንደሆነ ከኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገኙ ሪፖርቶች ማሳየታቸውን ቀጥለዋል።

በቅርቡ በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ እና በተባበሩት መንግስታት ትብብር የተዘጋጀ የድህነት መለኪያ ሪፖርት በኢትዮጵያ ውስጥ ከአስር ሰዎች ዘጠኙ በድህነት ይማቅቃሉ ማለቱን መዘገባችን ይታወሳል። ኒውስዊክ የተባለው ታዋቂ የአሜሪካ ጋዜጣ ከዛ ወዲህ ባወጣው ሪፖርትም፥ የመቶ አገሮችን የኑሮ ጥራት ደረጃ አነፃጽሮ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ውጤት በማግኘቷ 94ኛ ደረጃ ላይ እንዳኖራት ዘግበናል።

### ቢሳካለት ለአቅመ አዳም ከደረሰው ኢትዮጵያዊ . . . (ከገጽ 1 የዞሯል)

ይህን መግለጫ አስመልክቶ በስዊድን በስደተኝነት የሚኖሩ አንድ ኢትዮጵያዊ በሰጡን አስተያየት የራሱ የወያኔ ባለስልጣናት ዘመድ አዝማድ ስልጣንን መከታ በማድረግ ቪዛ እየወጣላቸውና በሃሰት የስደት ወረቀት ማግኘት የሚችሉበት የሃሰት ማስረጃ እየተፈበረከላቸው በሁሉም የአውሮፓና የአሜሪካ ሃገራት የጥገኝነት መጠያቂያ መስሪያ ቤቶችን ማጣበብ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። በዚህም የተነሳ በጥናቱ ላይ የተመለከተው 46 % እውነተኛውን አሃዝ ከሚገልጽ በታች ቢሆን እንጂ የሚያጠራጥር አይሆንም ብለዋል።

የዳብል ዲጂት እድገት እያሳየሁ ነው እንደኔ ያለ መንግስት የለም የሚለው ወያኔ የሚገዛት ኢትዮጵያ በዜጎቿ ስደተኝነት ከመንግስት አልባዋ ሶማሊያና የፖለቲካ ቀውስ አለባቸው ከሚባሉት የአፍሪካ ሃገራት በእጥፍ እንደሚበልጥ ይታወቃል።

## ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አጠቃላይ ጉባኤ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ መሆኑ ታወቀ

ግንቦት 7 ንቅናቄ በቅርቡ ሊያደርግ ላቀደው አጠቃላይ ጉባኤ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ መጀመሩ ታውቋል።

በዚህም አኳኋን በዚህ ሳምንት አውሮፓ ከሚገኙ አባላቱ ጋር የኤሌክትሮኒክ ስብሰባ በማካሄድ በአጠቃላይ ጉባኤው ላይ ለውይይት እንዲቀርቡ የሚፈልጓቸውን ሃሳቦች አሰባስቧል። ከግንቦት 7 አመራር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ እና አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል፤ እንዲሁም ከግንቦት 7 ጽህፈት ቤት ዶ/ር ታደሰ ብሩ በስብሰባው ላይ እንደተገኙ የታወቀ ሲሆን፤ ከሁለት ሰዓት ተኩል በላይ የፈጀ ሰፊ ውይይት መካሄዱን ተረድተናል።

በስብሰባው መጀመሪያ ላይ ማብራሪያ የሰጡት የግንቦት 7 ንቅናቄ ጽህፈት ቤት ሃላፊ ዶ/ር ታደሰ ብሩ፥ መጪው ጠቅላላ ጉባዔ ምናልባትም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወሳኝ የሆኑና በአገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ መሰረታዊ የሆነ ለውጥ የሚያመጡ ውሳኔዎች የሚተላለፉበት ይሆናል ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል።

የስብሰባው ተካፋዮች የድርጅቱን እንቅስቃሴ በሚመለከት እና ወደፊት ሊኖረው ስለሚገባው አካሄድ ያለምንም መቆጠብ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ በተበረታቱበት መሰረት በርካታ ጥያቄዎችን አቅርበዋል።

ግንቦት 7 በመጪዎቹ ሳምንታት ተመሳሳይ ስብሰባዎችን በሌሎች አህጉራት እንደሚያካሄድ የንቅናቄው የድርጅት ጉዳይ ጽህፈት ቤት ለዝግጅት ክፍላችን ገልጿል።

### የወያኔው የ5 አመት የኢኮኖሚ ልማት . . . (ከገጽ 1 የዞሯል)

ስለሆነም ስለ እድገት ስናወራ እነኝህ ወገኖች ኑሮአቸው ተሻሽሏል ወይስ እንደዚያው ነው፣ ማነቆዎች አሉባቸው ወይንስ የሉባቸውም የኑሮ ውድነት ከፍ ብሏል ወይንስ ዝቅ ብሏል? የሚሉትን ልንመዝን ይገባናል ብለዋል። ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ አብዛኛው ህዝብና ገበሬ ኑሮ እንደተመዘገበው እድገት ተሻሽሏል ለማለት አመላካች የሆኑ መረጃዎች የሉም፤ በምንም አይነት ልንክደው የማንቺለው ነገር ከ6 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ስር በሰደደ የውጪ ርዳት ድጋፍ እንዳሉ ተደጋግሞ ተነግሯል፤ ባለፈው ዓመት ኦክስ ፋም ባቀረበው ሪፖርት ደግሞ ከ13 ሚሊዮን የማያንስ ህዝብ ረሃብተኛ ነው ተብሏል። በመሆኑም እንቆቅልሹ ለግብርናው ዘርፍ እድገት አሳይቷል ሲባል መጋቢ የሆነው አስተዋጾ የሚያደርገው ክፍል ይሄው አርሶአደር በመሆኑ መሰረታዊ የማዋቅር ለውጥ ተደርጓል የሚለው ነገር ፉርሽ ይሆናል ማለት ነው ብለዋል።

የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎቹ በሌላም በኩል የአምስት ዓመቱ የትራንስፎርሜሽን እቅድ በአምስት ዓመት ኢትዮጵያን ከተረጂነት ለማላቀቅ ፍጹም አይቻልም፤ ተአምራዊ የሚባሉ ግኝቶች ካልተፈጠሩ በስተቀር የሚባለውን ለማመን ያዳግታል። ፈጽሞ ከውነታ የራቀ፤ በሃገሪቱ ያሉትን ነባራዊ ሁኔታዎች ያላገናዘበ፤ በዓለም ደረጃ ራሱ በጣም እያደጉ ናቸው የሚባሉ እንደ ቻይናና ህንድ ያሉ ሃገራትን ብንወስድ እነመለስ ዜናዊ አስመዘገብን የሚሉት 11 .5 % እድገት እንዴት ሊሆን እንደቻለ፤ በተለይም ዓለማቀቿን አሁን ካለቺበት የኢኮኖሚ ድቀት አንጻር ኢትዮጵያ በተጠቀሰው እድገት መጠን አደገች ሲባል መለኮታዊነትን የያዙ ይመስላል እንጂ ሊያሳምን የሚችል ነገር የለውም ብለዋል። በመጨረሻም ከመንግስት የሚቀርቡት መረጃዎች በፍጹም ተአማኒነት ያሎአቸው አይደሉም፤ ኢትዮጵያ ከዓለማችን በድህነት ሁለተኛ በህዝብ ብዛቷ ደግሞ ከአፍሪካ ሶስተኛ ሆና እያለች በምን አይነ ተአምር ይህ የታሰበ እቅድ እንደሚሳካ አይገባንም በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ረሰ አንቀጾቹን ጨምሮ በተለያዩ ፕሮግራሞቹ ይህ የወያኔ ሪፖርትም ሆነ እቅድ ምንም መሰረት የሌለውና መራባዊያንን ለማማለል የታቀደ እንጉርጉሮ እንደሆነ በተደጋጋሚ መግለጹ ይታወቃል።

### ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ . . . (ከገጽ 1 የዞሯል)

አንድም ተቃዋሚ ፓርቲ እንዳያልፍ በካድሬዎቹ አማካኝነት ገድቦ ከያዘ በኋላ 99.6% አግኝቻለሁ በማለት በቀድሞ የኮሚዩኒስት ሃገራት በስልጣን ላይ የነበሩ ባለ አንድ ፓርቲ ስራቶች ሲከተሉ የነበሩትን መንገድ ተግባራዊ አድርጓል። ለማወናበድና ለመቅጠፍ በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው እንግሊዝ ቦትስዋና ጃፓን አንድም ወቅት በንደዚህ አይነት ውጤት አሸነፍንበት ያሉበት ወቅት እንደሌለ ይታወቃል።

በቪኦኤ ጋዜጠኛ ወያኔ 99.6% አሸንፊያለሁ ስላለው ምርጫ የታዛቢ ቡድን ሪፖርት ተጠይቆ የሰራው ሴራ የተጋለጠበት መለስ ዜናዊ "የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ግምገማ ሪፖርት ቢዘገይም አያስጨንቀኝም ከዋናውና ማጠቃለያ ሪፖርታቸው በፊት ያቀረቡልኝ የመጀመሪያ ሪፖርት አያስደስትም እናም እንደ መረጃ ለመያዝም የሚየስደፍር አይደለም ብሏል። የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን በመጀመሪያ ግምገማ ሪፖርቱ የ2010ሩን ምርጫ ግልጽነት የጎደለው እና ዓለማቀፋዊ መስፈርቶችን የማያሟላ ነው ማለቱ ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org